## የኢትዮጵያ የምግብና የመድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን

# የአልኮል መጠጥ ማስታወቂያ እና ገላጭ ጽሁፍ ቁጥጥር መመሪያ 41/2011 ዓ.ም

ሰኔ 2011 ዓ.ም

## መግቢያ

በሀገሪቱ የአልኮል ተጠቃሚዎች ቁጥር እያደገ መምጣቱን እንዲሁም የአልኮል መጠጥን መጠቀም ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች አጋላጭ መሆኑ በጥናት ስለተረጋገጠ፤

ገደብ የሌለው የአልኮል ማስታወቂያ የአልኮል ተጠቃሚዎችን ቁጥር እንደሚጨምር በጥናት የተረጋገጠ ሲሆን ከቴክኖሎጂ መስፋፋት ጋር ተያይዞ የአልኮል ማስታወቂያ የስርጭት ስፋት፣ ይዘት፣ ዓይነት፣ የማስተላለፊያ መንገዶችንና ተደራሽነታቸውን ተገቢ በሆነ መንገድ መቆጣጠር በማስፈለጉ፤

የሚፈቀዱ የአልኮል ማስታወቂያ መልእክቶች በተጋነነና ተገቢ ባልሆነ መልኩ በማስተላለፍ በህብረተሰቡ ላይ የሚያስከትሉትን የስነ-ልቦና ጫና ለመከላከል፤ የአልኮል ማስታወቂያ ላይ የሚተላለፉት መረጃዎች ትክክለኛ መሆናቸውንና ለመቆጣጠርና በተሳሳተ መረጃ ምክንያት ሊደርስ ከሚችል ጉዳት ህብረተሰቡን መጠበቅ በማስፈለጉ፤

በአልኮል መጠጥ ማሸጊያ ላይ በአልኮል መጠጥ ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን የጤና ችግር አስቀድሞ እንዲገለጽ በማድረግ በጤና ላይ ሊያድርስ የሚችለውን ችግር ከወዲሁ መከላከል እንዲቻል፤

የኢትዮጵያ የምግብና የመድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን በምግብና መድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር1112/2011 አንቀጽ 71 (2) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአልኮል መጠጥ ማስታወቂያ እና ገላጭ ጽሁፍ ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 41/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) "የአልኮል መጠጥ" ማለት ማንኛውም የአልኮል ይዘቱ ከ 0.5 በመቶ በላይ የሆነ የመጠጥ ዓይነት ነው፤

2) "የአልኮል መጠጥ ምርት ማስተዋወቅ" ማለት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የአልኮል መጠጥን ወይም ተጠቃሚነትን ዓላማ ወይም ውጤት ያደረገ የማስተዋወቅ ማንኛውም የንግድ ግንኙነት፣ አስተያየት ወይም ድርጊት ነው፤

3) "ስፖንሰር ማድረግ" ማለት የአልኮል ምርትን ወይም አልኮል መጠጥን መጠቀምን የሚያበረታታ ሁነት፣ ድርጊት ወይም ግለሰብን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለዚህ ዓላማ መደገፍ ነው፤

4) "የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ" ማለት መገናኛ ብዙሃንን፣ የውጭ ማስታወቂያን፣ የቴሌኮምን፣ የፖስታ፣ የኢንተርኔት ድረ-ገፅ እና የፋክስ አገልግሎትን፣ ሲኒማን፣ ፊልምን፣ ቪዲዮን ወይም መሰል የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድን ይጨምራል፤

5) "በስፖንሰር የሚዘጋጅ ፕሮግራም" ማለት አንድን ፕሮግራም ወይም ዝግጅት እንዲካሄድ ወይም እንዲዘጋጅ ገንዘብ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተከፈለበት ወይም የክፍያ ቃል የተገባበት ፕሮግራም ወይም ዝግጅት ማለት ነው፤

6) "ቢልቦርድ" ማለት ተነጻጻሪ በሆነ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች በመጠቀም የሚቀርብ የማስታወቂያ መንገድን ጨምሮ በማንኛውም ህንጻ የውጭ ግድግዳ ላይ፣ በህንጻው ሌላ የውጭ ክፍል ላይ ወይም በራሱ በቆመ ማንኛውም መዋቅር ላይ ያለ ምርትን ለማስተዋወቅ የሚያገለግል የማስታወቂያ መንገድ ሆኖ በአልኮል መጠጥ ማከፋፈያ ወይም ችርቻሮ ንግድ ላይ በተሰማሩ ወይም አልኮል መጠጥ ለህብረተሰብ አገልግሎት በሚያቀርብ ድርጅት ቤት ወይም ህንጻ ላይ የተቋሙን ስያሜ ለመግለጽ ሲባል

በአባሪነት የሚሰቀል የአልኮል መጠጥ ምልክትን እና በህዝብ መጓጓዣ ትራንስፖርት ላይ የሚለጠፍ የአልኮል መጠጥ ማስታወቂያን ያጠቃልላል፤

7) "ገላጭ ጽሁፍ ማለት" ቁጥጥር በሚደረግበት ምርት ተቀዳሚ መያዣ ላይ ወይም መጠቅለያ ላይ የሚጻፍ የሚታተም ወይም የሚለጠፍ ሥዕል፣ ጽሁፍ ወይም ምልክት ነው፤
8) "የማስታወቂያ አስነጋሪ" ማለት በማስታወቂያ ማስተላለፊያ መንገድ አማካኝነት ምርቱ፣አገልግሎቱ፣ ስሙ፣ አርማው፣ ምልክቱ፣ አላማው ወይም ሌላ ተመሳሳይ መልዕክት የሚነገርለት ወይም የሚተዋወቅለት ሰው ነው፤
9) "የማስታወቂያ አስተላላፊ" ማለት በማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የአየር ጊዜ፣ የሕትመት ሽፋን ወይም መሰል አገልግሎት በመስጠት ማስታወቂያ የሚያስተላልፍ ሰው ነው፤
10) "የማስታወቂያ ወኪል" ማለት በማስታወቂያ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፤
11) "የብሮድካስት አገልግሎት" ማለት የሬዲዮ እና የቴሌቪዥን ሥርጭት አገልግሎት ነው፤
12) "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
13) ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አገላለጽ ሴትንም ይጨምራል፡፡

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ አልኮል መጠጥን በሚመለከቱ ማስታወቂያዎች እና የአልኮል መጠጥ ማሸጊያ ላይ በሚቀመጥ ገላጭ ጽሁፍና ምስል ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የአልኮል መጠጥን ማስተዋወቅ፣ ፕሮሞሺን እና ስፖንሰርሺፕ

### 4. ጠቅላላ

1) በአዋጅ ቁጥር 1112/2011 የአልኮል መጠጥን ማስታወወቅ፣ ፕሮሞት እና ስፖንሰር ማድረግ የተመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የአልኮል መጠጥ ማስታወቂያ ወይም ፕሮሞሽን ትክክለኛ፣ አሳሳች ያልሆነ፣ ተገቢ እና ስነ-ምግባርን የጠበቀ መሆን አለበት፡፡

2) ማንኛውም የተፈቀደ የአልኮል መጠጥ ማስታወቂያ በዚህ መመሪያ መሰረት የሚጠየቅ የጤና ማስጠንቀቂያ የያዘ ሆኖ ቢያንስ በአማርኛ ቋንቋ የቀረበ መሆን አለበት፡፡

## 5. የተከለከለ የአልኮል ማስታወቂያ

1) ማንኛውንም የአልኮል ምርት በብሮድካስት፣ በቢልቦርድ እንዲሁም የምርቱን ሽያጭ ከሎተሪ እጣ ወይም ከሽልማት ጋር በማንኛውም መንገድ በማያያዝ የሚደረግ የማስተዋወቅ ተግባር የተከለከለ ነው፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) መሰረት የአልኮል ምርትን ሽያጭ ከሎተሪ እጣ ወይም ከሽልማት ጋር በማያያዝ የሚደረግ የማስታወቂያ ወይም አሻሻጥ ስልት የአልኮል ምርትን በነጻ ወይም በሽልማት መልክ መስጠትን ጨምሮ እጣው ወይም ሽልማቱ የአልኮል ምርት ይሁን ከአልኮል ዉጭ የሌላ ማንኛውም ምርት ወይም አገልግሎት ይሁን የአልኮል ምርትን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚያስተዋዉቅ ተግባርን ያካትታል፡፡

3) ማንኛውም የአልኮል ምርት የንግድ ስም፣አርማ፣የንግድ ምልክት፣የድርጅት አርማ፣የንግድ መለያ ወይም ሌላ ተያያዥ መለያን የአልኮል ምርት ካልሆኑ ሌሎች ምርቶች፣ አገልግሎቶች ወይም ጉዳዮች ጋር በማያያዝ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ ቁርኝት እንዳላቸው በሚያሳይ መልኩ ማስተዋወቅ ወይም ፕሮሞት ማድረግ ክልክል ነው፡፡

4) ይህ መመሪያ ከመዉጣቱ በፊት የተሰቀሉ በአልኮል ንግድ ላይ በተሰማሩ ድርጅቶች ቤት ላይ የተሰቀሉ የዚህን መመሪያ መስፈርቶች የማያሟሉ ምልክቶች ይህ መመሪያው ከጸደቀበት ቀን እስከ 1 (አንድ) ወር ባለው ጊዜ ውስጥ መነሳት ይኖርባቸዋል፡፡

## 6. ገደብ የተደረገበት የአልኮል ማስታወቂያ

የዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ሌላ ባልተከለከለ የማስተዋወቂያ መንገድ የሚተላለፍ የአልኮል መጠጥ ማስታወቂያ፡-

1) የአዋቂነት፣ የታዋቂነት፣ ግላዊና ማህበራዊ ስኬትን እንደሚያስገኝ፣ ለተሻለ ሥነ ልቦናዊ ወይም አካላዊ ብቃት እንደሚጠቅም፣ የበሳልነት፣ በራስ የመተማመን ወይም የምርጥ ስብእና መለኪያ አደርጎ የሚያቀርብ፤

2) ለችግሮች መፍትሔ ሰጪ እንደሆነ ወይም አልኮል መጠቀም ከጭንቀት እንደ ሚያድን የሚያበረታታ ወይም የሚገልጽ፣

3) ከጤና እክል እንደሚፈውስ፣ እንደሚያበረታ ወይም እንደሚያነቃቃ የሚገልጽ፣

4) አካላዊ ጥንካሬ የሚሰጥ ወይም የሚያሻሽል በማድረግ የአልኮል ይዘታቸው ጠንካራ የሆኑ መጠጦችን መጠቀም ጥራቱን ወይም የተጠቃሚውን ደረጃ ከፍ የሚያደርገው አድርጎ የሚገልጽ፤

5) የአልኮል መጠጥ በመጠቀም እና ወሲብ ግንኙነት እንዳለው እንዲሁም አልኮል ተጠቅሞ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ ማድረግ፣ መኪና ማሽከርከር እንዲሁም ደህንነትን ለማረጋገጥ በጥንቃቄ የሚዘወሩ ሌሎች ማሽኖችን ላይ መስራት ተቀባይነት ያለው ተግባር እንደሆነ የሚያሳይ ወይም የሚገልጽ፤

6) ህፃናትን ወይም ታዳጊዎችን መሰረት ባደረገ ወይም ሞዴል በማድረግ፣ በተለምዶ ከህፃናት ጋር የተያያዘ የመጫወቻ ቁሳቁሶችን፣ ቀለሞችን፣ ታሪኮችን ወይም መሰል ድርጊቶችን ያካተተ፤

7) በዋናነት ለህፃናትን ወይም ለታዳጊዎች በተዘጋጀ ፕሮግራም ላይ የሚደረግ ቀጥተኛ ወይም ተዘዋዋሪ መንገድ የማስተዋወቅ ተግባር፤ እና

8) የአልኮል መጠጥ መጠቀም የወሲብ ብቃትን ወይም የፍቅር ግንኙነትን የሚያድስ አድርጎ የሚያሳይ ወይም የሚገልጽ መሆን የለበትም፡፡

## 7. የአልኮል መጠጥ ፕሮሞሺን

1) ማንኛውም ሰው ሀገራዊ ደራጃ የወጣለትን የአልኮል መጠጥ በዚህ መመሪያ እና ተፈጻሚነት ባለው ሌላ ህግ ከተደነገገው ውጭ ፕሮሞት ማድረግ የለበትም፡፡

2) ማንኛውም የባህል መጠጥን ጨምሮ ሀገራዊ ደራጃ የወጣለትን የአልኮል መጠጥ የፕሮሞሽን ቁሳቁስ ይዘት ስለ ምርቱ ይዘት፣ የጤና ጥቅም፣ በጤና ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ወይም የጎንዮሽ ጉዳት በሚመለከት አሳሳች በሆነ ወይም የተሳሳተ መረዳትን በሚፈጥር መንገድ መቅረብ የለበትም፡፡

3) በማንኛውም የንግድ ወይም ማህበራዊ አገልገሎት ዝግጅቶች ላይ እድሜያቸው ከ21 ዓመት በታች ለሆኑ ህፃናት ወይም ታዳጊዎች የአልኮል ምርት ምስል ወይም ጽሁፍ ያለበትን ቲሸርት፣ስቲከር፣ቁልፍ መያዣ፤ እና መሰል የፕሮሞሽን ቀሳቁስ መስጠት ወይም ማሰራጨት የተከለከለ ነው፡፡

4) ማንኛውም የአልኮል መጠጥ የፕሮሞሽን ቁሳቁስ ምርቱ ከ21 አመት በታች ለሆን ሰው መሸጥ ወይም ማቅረብ የተከለከለ መሆኑን የሚገልጽ በጉልህ ሊታይ የሚችል ጽሁፍ ወይም 21+ የሚል በጉልህ የሚታይ ቀለም ያለው ሎጎ መያዝ አለበት፡፡

## 8. የአልኮል መጠጥ ስፖንሰርሺፕ

1) ማንኛውም የተፈቀደ የአልኮል መጠጥ ማስታወቂያ በዋናነት ከ21 አመት በታች የሆኑ ህጻናት እና ታዳጊዎችን ማዕከል አድርጎ የሚዘጋጅ ዝግጅቶች በገንዘብ ወይም በዓይነት መደገፍ አይችልም፡፡
2) ሀገራዊ ደራጃ የወጣለትና የአልኮል ይዘቱ ከ10 በመቶ በላይ የሆነ የአልኮል መጠጥ አምራች፣አስመጪ ወይም አከፋፋይ የህዝብና የመንግስት በአላት እና ስብሰባ የንግድ ትርኢት፣ የስፖርት ውድድር፣ የትምህርት ቤት ዝግጅቶች እና ተመሳሳይ የሆኑ ሌሎች ወጣቶች የሚሳተፉበትን ኩነቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ስፖንሰር ማድረግ አይችልም፡፡
3) ማንኛውም ሀገራዊ ደረጃ የወጣለት ባህላዊ የአልኮል ምርት አምራች ወይም አከፋፋይ ድርጅት ማንኛውንም ኩነት ስፖንሰር ማድረግ አይችልም፡፡

## ክፍል ሦስት

## የአልኮል መጠጥ አስተሻሸግ እና ገላጭ ጽሁፍ

## 9. ጠቅላላ

1) ሀገር አቀፍ ደረጃ የወጣለት ለህብረተሰብ የሚቀርብ ማንኛውም የአልኮል መጠጥ ገላጭ ፅሁፍ የአልኮል መጠኑን፣ በተገቢ መንገድ ካልተጠቀሙ የጤና ችግር እንደሚያመጣ እንዲሁም አልኮል መጠቀም ጽንስን ሊጎዳ እንደሚችል በጉልህ በሚታይ ጽሁፍ የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡
2) የአልኮል ይዘቱ ከ10 በመቶ በታች የሆነ ሀገር አቀፍ ደረጃ የወጣለት ማንኛውም የአልኮል መጠጥ ገላጭ ፅሁፍ የአገልግሎት ጊዜውን መግለጽ ይኖርበታል፡፡
3) ሀገር አቀፍ ደረጃ የወጣለትና ለህብረተሰብ የሚቀርብ ማንኛውም የአልኮል መጠጥ ከ21 አመት በታች ለሆነ ሰው መሸጥ ወይም ማቅረብ የተከለከለ መሆኑን የሚገልጽ በጉልህ ሊታይ የሚችል ጽሁፍ ወይም 21+ የሚል ባለቀለም ሎጎ መያዝ አለበት፡፡

## 10. የጤና ማስጠንቀቂያ ይዘት

1) ሀገር አቀፍ ደረጃ የወጣለትና ለህብረተሰብ የሚቀርብ ማንኛውም የአልኮል መጠጥ ላይ የሚቀመጥ ማስጠንቀቂያ ከፊት፣ ከኋላ ወይም ከጎን ላይ ባለ ተቀዳሚ ማሸጊያ ላይ ሊቀመጥ የሚችል ሆኖ ቢያንስ የሚከተሉትን የጤና ማስጠንቀቂያ በአማርኛ ወይም እንግሊዝኛ ቋንቋ የያዘ ሆኖ "አልኮል መጠቀም ጽንስን ይጎዳል" "አልኮል መጠጥ የጤና ችግር ሊያመጣ ይችላል" እና "አልኮል ተጠቅሞ ማሽከርከር አደጋ ያመጣል" የሚሉ ማስጠንቀቂያዎችን መያዝ አለበት፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) ከተቀመጡት ሦስት ማስጠንቀቂያዎች ውስጥ "አልኮል መጠቀም ጽንስን ይጎዳል" እና "አልኮል ተጠቅሞ ማሽከርከር አደጋ ያመጣል" የሚሉት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያን በሚገባ የሚገልጽ ተያያዥ ባለቀለም ሎጎ ወይም ስዕላዊ መግለጫ ሊቀመጥ ይችላል፡፡

## 11. የጤና ማስጠንቀቂያ መጠን፣ አቀማመጥ እና ተያያዥ ጉዳዮች

1) የአልኮል መጠጥ ማስጠንቀቂያ፡-

ሀ. የማስጠንቀቂያውን መክበበያ ሳይጨምር በምርቱ ላይ ከተቀመጠው አጠቃላይ የፊት፣ የኋላ ወይም የጎን የሌብል ስፋት ቢያንስ ከ20% ያላነሰ ቦታ የሸፈነ፤

ለ. ጽሁፉ የሚያርፍበት የውጭ ማሸጊያ እይታን ሊደብቅ በማይችል ሁለት ተቃራኒ ቀለም የሆነ፤

ሐ. በማሸጊያው ላይ የሚያስቀመጥ ሌላ ምርቱን የሚመለከት የተፈቀደ ማንኛውም መረጃ መሸፈን ወይም እይታውን የማይከልል፤

መ. የአልኮል መጠጥ ከ21 አመት በታች ለሆነ ሰው የተከለከለ መሆኑን የሚገልጽ ጽሁፍ ወይም ባለቀለም ሎጎን ጨምሮ በአንቀጽ 10 መሰረት የሚቀመጡ ማስጠንቀቂያዎች ከሌላ ምርቱን ማንኛውም መረጃ ጋር ሳይቀላቀል በአንድ ላይ የተቀመጡ እና ከሌሎች መልእክቶች ለመለየት በሳጥን ወይም ሌላ ተነጻጻሪ መክበቢያ ውስጥ የተቀመጠ፤

ሠ. በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጻፈ፤

መሆን አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) (ሀ) መሰረት የጤና ማስጠንቀቂያው መጠን የሚሰላው ከምርቱ የፊት፣ የኋላ ወይም የጎን ገጽ ላይ ከሚቀመጠው ሌብል ገላጭ ጽሁፍ የከፍተኛውን የሌብል ስፋት በመውሰድ ይሆናል፡፡

3) የአልኮል መጠጡ መረጃ የተቀመጠው በሚለጠፍ ገላጭ ጽሁፍ ላይ ሳይሆን የምርቱ ማሸጊያ አካል ሲሆን በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) (ሀ) መሰረት የሚቀመጥ የማስጠንቀቂያ መጠን የሚሰላው ሌላ ምርቱን የሚመለከት መረጃ ከተቀመጠበት የምርቱ የፊት፣ የኋላ ወይም የጎን ገጽ ከፍተኛውን በመውሰድ ይሆናል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) (መ) መሰረት የሚቀመጥ የአልኮል መጠጥ ማስጠንቀቂያ የጽሁፍ እና የስእል መጠን ማሳነስ የተከለከለ ሲሆን ጽሁፉ እና የስእል መግለጫዉ የሳጥኑን ወይም ሌላ ተነጻጻሪ መክበቢያ ውስጥ ያለን ቦታ ሙሉ ለሙሉ መጠቀም ያለበት ሆኖ በመልእክቶቹ መካከል ያለ ክፍተት ምክንያታዊ ያልሆነ መሆኑን የማረጋገጥ ሀላፊነት የአልኮል አምራቹ ወይም አስመጪው ይሆናል፡፡

5) በአልኮል መጠጥ ላይ የሚቀመጥ ማስጠንቀቂያ የምርቱ ማሸጊያ አካል ካልሆነ ወይም የሚለጠፍ ገላጭ ጽሁፍ ከሆነ ገላጭ ጽሁፉ በቀላሉ ከማሸጊያው ላይ ሊለቅ በማይችል ሁኔታ መለጠፍ አለበት፡፡

6) ይህ አንቀጽ መመሪያው ከጸደቀበት ከ180 ቀናት በኋላ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 12. ኃላፊነት

1) ማንኛውም የማስታወቂያ አስነጋሪ፣ አስተላላፊ፣ የማስታወቂያ ወኪል ወይም አግባብ ያለው ሌላ ሰው ይህን መመሪያ የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

2) በዚህ መመሪያ መሰረት ማንኛውንም የአልኮሆል ምርት ማስታወቂያ በሚመለከት የማስታወቂያ አስነጋሪው ወይም የማስታወቂያ አሰራጭ፤ ፕሮሞሽን ወኪልን ጨምሮ ማንኛውም የፕሮሞሽን ቁሳቁሶቹን ያሰራጨ ወይም እንዲሰራጭ ያደረገ ሰው በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መስፈርቶችን ማክበሩን የማረጋገጥ የነጣላ እና የጋራ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## 13. መረጃ ይዞ ስለማቆየት

1) ማንኛውም የማስታወቂያ አስተላላፊ የአንድን የተላለፈ ማስታወቂያ ቅጂ ሪኮርድ ቢያንስ ለስድስት ወር ይዞ ማቆየት ይኖርበታል፡፡
2) በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) መሰረት የተያዘ መረጃ አግባብ ያለው አካል የማስታወቂያ ሪኮርድ ቅጂ እንዲቀርብለት ሲጠይቅ በራሱ ወጪ ማቅረብ አለበት፡፡

## 14. የመተባበር ግዴታ

ባለስልጣኑ ይህን መመሪያ ለማስፈፀም እንዲችል ጉዳዩ የሚመለከተው ማንኛውም የፌዴራልና የክልል መንግሥት አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## 15. ቅጣት

ይህንን መመሪያ ተላልፎ የሚገኝ ማንኛውም ሰው ዘርፉ በሚመራበት ስለምግብና መድኃኒት አስተዳደር የወጣ አዋጅ ቁጥር 1112/2011 እና በሌሎች አግባብ ያላቸው የሀገሪቱ ሕጎች መሰረት ይቀጣል፡፡

## 16. ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች

ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 17. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሰኔ 10 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ሄራን ገርባ**

**የኢትዮጵያ የምግብና የመድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን**

**ዋና ዳይሬክተር**